DEPARTMENT OF HEALTH

# የሄፓታይተስ B መረጃ ለእርጉዝ ሴቶች

## ሄፓታይተስ B ምንድን ነው?

- ሄፓታይተስ B የጉበት በሽታ ሲሆን የሚፈጠረውም በቫይረስ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ በ ሄፐታይተስ B የሚያዙ ሰዎች ቫይረሱ በሰውነታቸው ውስጥ የሚቆይ ሲሆን ይህም ህይወታቸውን በሙሉ ለሚቆይ ህመም ይዳርጋቸዋል፡፡
- ሄፓታይተስ B በጊዜ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የጤና ችግር ሊያስከትል ይችላል ይህም የጉበት መጎዳትን፣ የጉበት ስራ ማቆምን እና የጉበት ካንሰርን ጨምሮ ነው፡፡
- አብዛኛዎቹ ሄፓታይተስ B ያለባቸው ሰዎች ምንም ምልክት የማየታይባቸው ሲሆን እንዳለባቸው ላያውቁ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ይህንን ሄፓታይተስ B ወደሌሎች ሊያስተላልፉ ይችላሉ፡፡

## እርጉዝ የሆኑ ሴቶች መመርመር ያለባቸው ለምንድን ነው?

- አንዲት እርጉዝ የሆነች ሴት ሄፓታይተስ B እንዳለበታ ተመርምራ የምታውቅ ከሆነ፣ ልጅዎ በወሊድ ጊዜ ህክምና ያስፈልገዋል፡፡ በሚወለዱበት ወቅት ህክምናውን የሚያገኑ ህጻናት በሄታይተስ B የመያዝ እድላቸው ጠባብ ነው፡፡
- ህጻናት በ ሄፓታይተስ B በሚያዙበት ወቀት በህይወት ዘመናቸው በሙሉ የሚቆይ ህመም ሊያስከትልባቸው ይችላል፡፡
- እርጉዝ ሴቶች የ ሄፓታይተስ B ምርመራን በእያንዳንዱ የእርግዝናቸው ወቅት ሊያደርጉ ያስፈልጋል፡፡

## እርጉዝ ሆነሽ በ ሄፓታይተስ B ከተያዝሽ ምን ማድረግ አለብሽ?

- የጤና አገልግሎት አቅራቢሽን በማግኘት ስለ ሄፓታይተስ B ምን ማድረግ እንደሚያስፈልግሽ ማወቅ አለብሽ፡፡
- ሄፓታይተስ B ወደልጅሽ እንዳይተላለፍ ይሆን ዘንድ የሚሰጡ ህክምናዎች አሉ፡፡
- ሄፓታይተስ B እንዳለብሽ የማታውቂ ከሆነ፣ ጤና አገልግሎት አቅቢሽ የ ሄፓታይተስ B ደም ምርመራ እንዲያደርግልሽ ጠይቂ፡፡

## ልጅሽ እንዳይያዝ እንዴት መከላከል ትችያለሽ?

- በእያንዳንዱ እርግዝና ወቅት የ ሄፓታይተስ B ምርመራ አድርጊ፡፡
- ምርመራሽ ሄፓታይተስ B እንደሌለ የሚያሳይ ከሆነ፣ ስለ ሄፓታይተስ B ክትባጥ ጠይቂ፡፡
- ምረመራሽ ሄፓታይተስ B እንዳለ የሚያሳይ ከሆነ፣ ልጅሽ ህክምና እና ክትትል ያስፈልገዋል፡፡:
    - ከወሊድ በኋላ ልጅሽ የተከታታይ ክትባቱን የመጀመሪያ ክፍል እና የሄፓታይተስ B ኢሚዩን ግሎቢንን (HBIG) ይወስዳል፡፡
    - ልጅሽ ይህንን ሄፓታይተስ B ተከታታይ ክትባት መጨረስ ያስፈልገዋል፡፡
    - ተከታታይ ከሆነው ክትባት በኋላ፣ ዶክተርሽ የደም ናሙና በመውሰድ ልጅሽ በ ሄፓታይተስ B ከመያዝ የተጠበቀ አንደሆነ ያረጋግጣል፡፡
- ሄፓታይተስ B ቢኖርብሽም ጡት ማጥባት ትችያለሽ፡፡

Minnesota Department of Health
Perinatal Hepatitis B Prevention Program
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164
651-201-5414, 1-877-676-5414
www.health.state.mn.us/hepatitis

Hepatitis B Information for Pregnant Women – Amharic (2/2016)

*To obtain this information in a different format, call: 651-201-5414.*